የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ሐምሌ 25/2000

# በቀድሞ እስረኞች ስም ሊነገድ ዕቅድ ተዘጋጅቷል

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ኮሚቴ በቅርቡ ባገኘው መረጃ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ “የቀድሞ እስረኞ ች ድምፅ” በሚል ተቋም መስርቶ በዚህ ሽፋን የዘመነ ደርግ እስረኞችን ሰቆቃ ሊነግድበት ማቀዱ ተጋልጧል፡፡ ይህ ሙከራ ከዚህ በፊትም ተጀምሮ መክሸፉ የሚታወቅ ነው፡፡

የዘመነ ደርግ እስረኞች በአብዛኛው ኢሕአፓ ተብለው መከራ የተቀበሉ ሲሆኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢሕአፓ ላይ ዘምቶ ዛሬም ብዙ የኢሕአፓ አባላትን በእስር የያዘና ደብዛቸውን ያጠፋ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም፣ በቀይ ሽብር ሰለባዎችና በቀድሞ እስረኞች ዙሪያ የሚረጨው የአዞ እንባ አሰቃቂ ቧልት ከመሆን የሚያልፍ አይደለም፡፡ ገሎ ማልቀስና ሙሾ ማውረድ የሰብዓዊ መብት ረጋጮች አሳፋሪ ልምድ ሆኖ በሀገራችን የታየ በመሆኑ አገዛዙ ለቀድሞ እስረኞች የተቆረቆረ መስሎ በስማቸው ከዚህም ከዚያም ገንዘብ ለመሰብሰብ መነሳቱና በሰው ቁስል እንጨት እየሰደደ ሊያተርፍ ማቀዱን ኢፖእአኮ በጥብቅ ያወግዛል፡፡ የቀድሞ እስረኞች ድምፅ የሚባለውም የአገዛዙ ድምፅ ከመሆን አያልፍምና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዚህ እንዳይደናገር ከዛሬው ኢፖእአኮ ያጋልጣል፡፡

የወያኔ ቡድን ለኢሕአፓ ስቃይ ቅንጣት ደንታ ካለው በእጁ ያሉትን የኢሕአፓ መሪዎችና አባላት በአስቸኳይ ይልቀቅ ወይም የደረሱበትን/ያደረሰባቸውን ያሳውቅ፡፡ የሕዝብን ሰብዓዊ መብት ማክበር ይጀምር፡፡ አሊያ ገሎ ለቅሶ፣ አስሮና ደብዛ አጥፍቶ ሙሾ ሕዝብን ዳግም ለማጭበርበር መጣር ነውና ሊወገዝ ይገባዋል፡፡ ሁሉም ዜጋ በተለይም የቀድሞ እስረኞች በያሉበት ይህንን የወያኔ አገዛዝ ዕቅድ እንዲያጋልጡና እንዲቃወሙ አፖእአኮ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE